# ወርሃዊ የወላጅ ድጎማ ፕሮግራም የተማሪዎች ትራንስፖርት ክፍል

የስቴቱ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽህፈት ቤት እንደ ተጨማሪ የመጓጓዣ አማራጭ የወላጅ ድጎማ ፕሮግራም ያቀርባል። ፕሮግራሙ ከOSSE-DOT ከሚቀርበው የመኪና ወይም የአውቶቡስ አገልግሎት መርጠው ለሚወጡ እና ተማሪዎቻቸውን በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት በራሳቸው ለሚያጓጉዙ ብቁ የሆኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወርሃዊ ድጎማ ይሰጣል። ይህ በተጨማሪ ተማሪው ከትምህርታቸው ጋር በተያያዙ ልዩ አገልግሎቶች ላይ ተማሪን ማምጣት እና መውሰድን ይጨምራል። እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸው ብቁ ቤተሰቦች ተማሪዎችን በራሳቸው ማጓጓዝ እንዲችሉ ለመደገፍ በወር $400 ያገኛሉ።

## ለወርሃዊ ድጎማ ፕሮግራሙ ብቁ የሚሆነው ማነው?

- ለትራንስፖርት ብቁ የሆኑ እና የእነርሱ LEA የትራንስፖርት ጥያቄ ቅጽ (TRF) ያቀረቡላቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በፕሮግራሙ ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ።

## ወርሃዊ የወላጅ ድጎማ ፕሮግራም ለወላጅ/አሳዳጊ የመጓጓዣ ወጪዎች ምን ያህል ይሰጣል?

- ወርሃዊ የወላጅ ድጎማ ለተፈቀደላቸው የፕሮግራም ተሳታፊዎች በወር $400 ቋሚ ክፍያ ይሰጣል።

## በወርሃዊ የወላጅ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ለመመዝገብ ጥያቄውን ማን ሊያነሳ ይችላል?

- ትክክለኛ እና ተገቢ የሆነ የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በተማሪው ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገበ የተማሪው ሕጋዊ ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሳዳጊ ወይም ሌላ ዋና አሳዳጊ ብቻ ነው።

## መቼ ነው ወላጅ/አሳዳጊ በወርሃዊ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ መመዝገብ የሚችሉት?

- በወርሃዊው የወላጅ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ በፈቃደኝነት የሚከናወን ሲሆን በOSSE-DOT ድር ጣቢያ በ https://data.osse.dc.gov/dot-parent-stipend/ ላይ የሚገኘውን የምዝገባ ቅጽ በመሙላት ክፍት በሆነው የማመልከቻ ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ መመዝገብ ይቻላል።

## ለመሳተፍ የሚያስፈልጉት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

- ለተማሪው በፋይል ውስጥ TRF መኖር አለበት።
  የተማሪው ትምህርት ቤት ለተማሪው በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ለመጠየቅ ቅጽ ማቅረብ አለበት።
- ተማሪው በየወሩ 70 በመቶ የሚሆኑትን የትምህርት ቀናት መከታተል አለበት።
- ወላጅ የW9 ቅጽ ማቅረብ አለበት።
- ወላጅ የዋና አቅራቢ ቅጽ ማቅረብ አለበት።
- እንደ አማራጭ ወላጅ/አሳዳጊው በቀጥተኛ ተቀማጭ በኩል ክፍያ ለመቀበል የአውቶማቲክ ክሊሪንግ ሃውስ (ACH) ቅጽ ማቅረብ ይችላሉ። **ቀጥተኛ ተቀማጭ እንዲጠቀሙ እና**

**ወላጆች/አሳዳጊዎች** የባንክ ስም፣ የባንክ አድራሻ፣ የሂሳብ ስም፣ የሂሳብ ቁጥር እና የባንክ ራውቲንግ ቁጥርን የሚያረጋግጥ ባዶ ቼክ **ወይም** የባንክ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ አጥብቀን እናበረታታለን።

**አንድ ተማሪ በአሁኑ ጊዜ የአውቶቡስ አገልግሎት የማይጠቀም ወይም የማያገኝ ከሆነ ወላጁ በፕሮግራሙ ውስጥ መሳተፍ አይችልም ማለት ነው?**

- የተማሪው IEP ተማሪው የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ለመቀበል ብቁ መሆኑን በሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት እና የተማሪው ትምህርት ቤት አገልግሎቶችን ለመጠየቅ ለOSSE DOT የትራንስፖርት መጠየቂያ ቅጽ (TRF) ማቅረብ አለበት። እነዚህ ሁለት መስፈርቶች ካልተሟሉ ቤተሰቡ በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ብቁ አይሆንም።

**አንድ ተማሪ በየወሩ 70 በመቶ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት መስፈርትን የማያሟላ ከሆነስ?**

- ተማሪዎች በየወሩ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት አፈፃፀም ግምገማ ይደረግባቸዋል። ይህ ግምገማ የሚከናወነው ትምህርት ቤቱ በትምህርት ገበታ የመገኘት መረጃውን እንዲያስገባ ለማስቻል ከየወሩ መጨረሻ ከ10 ቀናት በኋላ ነው። አንድ ተማሪ በአንድ ወር ውስጥ ከ70 በመቶ በላይ የትምህርት ቀናትን ካመለጠው የገንዘብ ድጎማ አይሰጥም። ለሕክምና ወይም ለሌሎች የተፈቀዱ ምክንያቶች የሚኖሩ መቅረቶች ከ70 በመቶው መስፈርት ጋር አይቆጠሩም።

**የዋና አቅራቢ ቅጽን እንዴት መሙላት እችላለሁ?**

- የዋና አቅራቢ ቅጽ ቅጂ አገናኝ በማመልከቻው ላይ ይገኛል። የሚያስፈልጉ መስኮች በቢጫ ቀለም ጎላ ብለው ተለይተዋል። ሁሉንም አስፈላጊ መስኮች ይሙሉ። "የግብር መታወቂያ (Tax ID)" መስክ ውስጥ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ያስገቡ። "የአቅራቢ/ሻጭ/የባለቤትነት አይነት (Supplier/Vendor/Ownership Type)" ለእርስዎ ይሞላል።

**ወላጅ/አሳዳጊ ምዝገባን እንዴት ያቆማል?**

- ማቋረጥ የሚቻለው ማመልከቻው ከተፈቀደ በኋላ ብቻ እና ከዚያ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ነው። በፕሮግራሙ ያላቸውን ምዝገባ ለማቋረጥ እና በOSSE ወደ ሚቀርቡ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ለመመለስ ህጋዊ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡
    - በተማሪው ስም ክፍል ውስጥ በሚገኘው ማመልከቻ ውስጥ "አቋርጥ (Discontinue)" የሚለውን አማራጭ ይምረጡ።
    - ወላጅ/አሳዳጊው የፕሮግራም ምዝገባቸው መቋረጡን ለማረጋገጥ በስርዓቱ የተፈጠረ የኢሜይል መልዕክት ይቀበላሉ።
    - ወላጅ/አሳዳጊው አዲስ TRF ለOSSE-DOT እንዲቀርብ ለመጠየቅ የተማሪውን ትምህርት ቤት ማነጋገር አለባቸው።
- የOSSE የትምህርት ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት ወዲያውኑ እንደማይጀመር እና መልሶ ለመጀመር እስከ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ሊወስድ እንደሚችል እባክዎ ልብ ይበሉ። በዚህም ምክንያት ወላጆች የOSSE አገልግሎት መልሶ እስከሚጀምር ድረስ በራሳቸው ማጓጓዝ መቀተል ይኖርባቸዋል።

**በፕሮግራሙ ያለኝን ምዝገባ ካቋረጥኩ የOSSE የትምህርት ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት እንደገና እስኪጀመር ድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

- የትምህርት ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት የሚጀምረው የተማሪዎ ትምህርት ቤት TRFን ለOSSE-DOT ሲያቀርብ ነው። ምዝገባዎን ከማቋረጥዎ በፊት እባክዎ ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ። የOSSE የትምህርት ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት ወዲያውኑ አይጀምርም እናም ለመጀመር እስከ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ሊወስድ ይችላል። በዚህም ምክንያት ወላጆች የOSSE አገልግሎት መልሶ እስኪጀምር ድረስ በራሳቸው ማጓጓዝ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

**ምዝገባዬን ካቋረጥኩ በኋላ እንደገና ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት መምረጥ እችላለሁ?**

- አይ፣ ማመልከቻው ከተፈቀደ በኋላ ተሳትፏቸውን የሚያቋርጡ ተሳታፊዎች እንደገና ለማመልከት እስከሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ድረስ መጠበቅ አለባቸው።

**ከተመዘገቡ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪያቸውን ወደ ትምህርት ቤት ማጓጓዝ የማይችሉበት ድንገተኛ አደጋ ወይም የመጨረሻ ደቂቃ ክስተት ሲፈጠር ምን ማድረግ አለባቸው?**

- ወላጆች/አሳዳጊዎች እራሳቸው ለማጓጓዝ ከመረጡ በኋላ፣ ተማሪዎቻቸውን በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እና ወደ ቤት የማመላለስ ሃላፊነት እንደሚወስዱ ልብ ሊባል ይገባል። የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች መርጠው እንዲገቡ እና ከፕሮግራም ምዝገባ እንዲወጡ ተፈቅዶላቸዋል፣ ሆኖም ግን፣ የ OSSE የትምህርት ቤት አውቶቡስ መጓጓዣን ወደነበረበት መመለስ ከተማሪው ት/ቤት TRF ከደረሰ በኋላ ለ10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት መደበኛ የሥራ ማስኬጃ ጊዜ ተገዢ ነው።

**በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ቤተሰቦች በፕሮግራሙ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው?**

- አዎ። በእያንዳንዱ የትምህርት አመት መጨረሻ ላይ ምዝገባ ወዲያውኑ ይቋረጣል። ይሁን እንጂ OSSE ለፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በየዓመቱ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት ስለ ክፍት የምዝገባ ጊዜ ለማሳወቅ ማስታወቂያ ይልካል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪ የትምህርት ቦታ ከተወሰነ በኋላ አዲሱ የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት ማመልከቻውን እንደገና ማቅረብ ይችላሉ።

**በተራዘመ የትምህርት ዘመን (ESY) ወቅት ወርሃዊ የድጎማ አማራጩ ይቀርባል?**

- OSSE-DOT የፕሮግራሙን ቀጣይነት ለማስታወቅ በበጋው ወራት ESY ከመጀመሩ በፊት ለወላጆች ማስታወቂያ ይልካል።

**አመልካቾች ማመልከቻቸው እንደተፈቀደ እንዴት ያውቃሉ?**

- አመልካቾች ማመልከቻው ከታየ በኋላ ያለበትን ሁኔታ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ በኢሜይል አማካኝነት ይደርሳቸዋል። የጽሑፍ ማስታወቂያው ቀጣይ እርምጃዎችን እና የራስ-መጓጓዣ መቼ እንደሚጀመር ግልጽ መመሪያዎችን ይሰጣል። ይህ ሂደት እስከ 30 ቀናት ሊወስድ ይችላል።

**ክፍያ የሚከፈለው እንዴት ነው?**

- OSSE DOT በየወሩ ክፍያዎችን በቼክ ወይም በቀጥተኛ ተቀማጭ ይፈጽማል።
    - ክፍያን በወረቀት ቼክ ለመቀበል የሚመርጡ ወላጆች ክፍያውን በዩ.ኤስ. ፖስታ በኩል ይቀበላሉ። ይህ አማራጭ ሲመረጥ፣ OSSE በአመልካቹ W-9 ቅጽ ላይ የቀረበውን መረጃ የወረቀት ቼክ መስጠትን ለማመቻቸት ይጠቀማል። የወረቀት ቼክ ለመቀበል ተጨማሪ እርምጃ አያስፈልግም።
    - በተጨማሪም ወላጆች በቀጥታ ወዳቀረቡት የባንክ ሂሳብ በሚተላለፍ ተቀማጭ አማካኝነት ክፍያ ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ። ይህ አማራጭ ሲመረጥ ወላጅ የአውቶማቲክ ክሊሪንግ ሃውስ (ACH) ቅጽ መሙላት እና የባንክ ስም፣ የባንክ አድራሻ፣ የሂሳብ ስም፣ የሂሳብ ቁጥር እና የባንክ ራውቲንግ ቁጥርን የሚያረጋግጥ ባዶ ቼክ **ወይም ደግሞ** በባንክ የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው። ለቀጥተኛ ተቀማጭ ክፍያ ብቁ የሆኑት የዩ.ኤስ. ባንኮች ብቻ ናቸው። የውጭ የባንክ ተቀማጭ ሂሳቦች ተቀባይነት የላቸውም። የቀጥተኛ ተቀማጭ ቅጾች በማመልከቻው ውስጥ ካልተቀረቡ በነባሪ ክፍያ በወረቀት ቼክ ይፈጸማል። **ይህ አማራጭ የዩ.ኤስ. ፖስታ መዘግየቶችን ለማስወገድ በጥብቅ ይበረታታል።**

**ወላጆች/አሳዳጊዎች የW-9 የግብር ቅጽ መሙላት የሚጠበቅባቸው ለምንድን ነው?**

- W-9 በዲሲ ከተማ አቀፍ የክፍያ ስርዓት ውስጥ የክፍያ መዝገብ ለመመስረት ያስፈልጋል፣ ይህም OSSE ወርሃዊ ክፍያዎችን እንዲያከናውን ያስችለዋል። OSSE-DOT ወላጆች/አሳዳጊዎች የድጎማ ክፍያውን መቀበል የሚያስከትለውን ማንኛውም የግብር ተፅዕኖ ለመወሰን ከCPA ጋር እንዲመክሩ ያበረታታል።

**አመልካች የማህበራዊ ዋስትና ቁጥራቸውን ማቅረብ አለባቸው?**

- አዎ። ማመልከቻውን ከክፍያ መዝገብ ጋር ለማገናኘት የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሩ ያስፈልጋል። OSSE የዚህን መረጃ አጠቃቀም እና ጥበቃ በተመለከተ ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች እና ደንቦች ይከተላል።

**ህጋዊ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ተንከባካቢ የወላጅ ክፍያ ፕሮግራሙን እና የወርሃዊ ድጎማ ፕሮግራሙን በተመሳሳይ ጊዜ መጠቀም ይችላሉ?**

- አይ፣ ወላጅ/አሳዳጊው በሁለቱም ፕሮግራሞች በተመሳሳይ ጊዜ መመዝገብ አይችሉም።

**ወላጅ/አሳዳጊ በቤተሰቡ ውስጥ ብዙ ብቁ ተማሪዎች ካሏቸው ከአንድ በላይ ድጎማ ሊያገኙ ይችላሉ?**

- አዎ። ወላጅ/አሳዳጊ ከአንድ በላይ ተማሪዎችን በራሳቸው ለማጓጓዝ መምረጥ ይችላሉ። ማመልከቻው ከፀደቀ በኋላ ወላጅ ለእያንዳንዱ የተፈቀደለት ተማሪ የድጎማ ክፍያ ያገኛሉ።

**አንድ ወላጅ/አሳዳጊ የOSSE የትራንስፖርት አገልግሎቶችን የሚጠቀሙ በርካታ ልጆች ካሉት፣ ሌሎቹ ተማሪዎች የOSSE የትራንስፖርት አገልግሎቶችን መጠቀማቸውን ሲቀጥሉ አንድ ተማሪ በድጎማ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ይችላል?**

- አዎ። ወላጅ/አሳዳጊው በራሳቸው ማጓጓዝ የሚፈልጉትን ተማሪ ስም በማመልከቻው ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ወላጅ አንድ ተማሪ የOSSE ትራንስፖርት አገልግሎቶችን መጠቀሙን እንዲቀጥል ከፈለጉ፣ የዚህን ተማሪ ስም በማመልከቻው ውስጥ ማስገባት ***የለባቸውም***።

**በወርሃዊ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ ሊከለከል ይችላል?**

- አዎ። አንድ ማመልከቻ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊከለከል ይችላል፡
    - ከሚያስፈልጉት ቅጾች ውስጥ ማናቸውም ሃሰተኛ፣ ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ መረጃ ከያዙ
    - አስፈላጊዎቹ ቅጾች የተጠናቀቁት ወይም የተላኩት በተማሪው ትምህርት ቤት ውስጥ ከተመዘገበው ሕጋዊ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ዋና ተንከባካቢ በተለየ ሌላ ሰው ከሆነ
    - ተማሪው/ዋ የትራንስፖርት ብቁነት መስፈርት አላሟላም/ችም
    - ማመልከቻው ድርብ ግቤት ከሆነ
    - ፕሮግራሙ ከፍተኛው የተሳታፊዎች ቁጥር ላይ ከደረሰ

**የአንድ ተሳታፊ ወርሃዊ ድጎማ በ OSSE-DOT ሊከለከል ይችላል?**

- አዎ። ተማሪዎች በየወሩ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት አፈፃፀም ግምገማ ይደረግባቸዋል። ይህ ግምገማ የሚከናወነው ትምህርት ቤቱ በትምህርት ገበታ የመገኘት መረጃውን እንዲያስገባ ለማስቻል ከየወሩ መጨረሻ ከ10 ቀናት በኋላ ነው። አንድ ተማሪ በአንድ ወር ውስጥ ከ70 በመቶ በላይ የትምህርት ቀናትን ካመለጠው የገንዘብ ድጎማ አይሰጥም። ለተፈቀዱ ምክንያቶች የሚኖሩ መቅረቶች ከ70 በመቶው መስፈርት ጋር አይቆጠሩም። ስለሁኔታው ለማሳወቅ ለወላጅ/አሳዳጊው ማሳወቂያ ይላካል።

**ወላጆች ወርሃዊ ድጎማዎቹን የሚቀበሉት መቼ ነው?**

- ወርሃዊ የድጎማ ክፍያዎች የሚከናወኑት እና የሚከፈሉት ትራንስፖርቱ ከተከናወነበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር ነው (ለምሳሌ የሴፕቴምበር ድጎማ የሚከፈለው በኦክቶበር ወር ነው)። ትምህርት ቤቱ በትምህርት ገበታ የመገኘት መረጃውን እንዲያስገባ ለማስቻል ከየወሩ መጨረሻ ከ10 ቀናት በኋላ እና በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ግምገማ ከተከናወነ በኋላ ድጎማው ይከፈላል።
  ከቀጣዩ ወር አጋማሽ ባልበለጠ ክፍያ ሊጠበቅ ይችላል። በቀጥተኛ ተቀማጭ መልክ የሚተላለፉ ክፍያዎች በዩ.ኤስ. ፖስታ በኩል ከሚላኩት የወረቀት ቼኮች በበለጠ ፍጥነት እንደሚደርሱ ያስታውሱ። በዩ.ኤስ. ፖስታ መላኪያ ሂደት ምክንያት ለሚከሰቱ መዘግየቶች OSSE-DOT ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ወላጆች ቀጥተኛ ተቀማጭ አማራጭን እንዲመርጡ እናበረታታለን።

**ወርሃዊ ድጎማዬ ያልደረሰኝ ለምንድን ነው?**

- ወርሃዊ ድጎማ ላይደርስ የሚችልባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። ተማሪው የ70 በመቶ በትምህርት ገበታ የመገኘት መስፈርቱን ማሟላት ካልቻለ ወላጁ ለዚያ ወር የሚሰጠውን የድጎማ ክፍያ ለማግኘት ብቁ አይሆንም። በማመልከቻዎ ላይ የተሳሳተ አድራሻ ወይም የባንክ ሂሳብ መረጃ ሊኖር ይችላል። በዩ.ኤስ. ፖስታ አላላክ ሂደት ውስጥ የወረቀት ቼክ ጠፍቶ ሊሆን ይችላል። ለሌሎች ክስተቶች ምክንያታቸውን ለመወሰን በOSSE-DOT ሰራተኞች ሊመረመሩ ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ክፍያ ለመጠየቅ ለ osse.stipendapp@dc.gov ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

**ማመልከቻዬን ለማስገባት ጥያቄ ካለኝ ወይም ችግር ካጋጠመኝ ማንን አነጋግራለሁ?**

- የወላጅ ድጎማ ፕሮግራሙን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በሙሉ በኢሜይል ለ osse.stipendapp@dc.gov ሊላኩ ይችላሉ።